የሰበር መ.ቁ. 22621

ግንቦት 30 ቀን 1998

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ዓለም ኃይሉ

ተጠሪ፡- አቶ ጥላሁን ሃይለሥላሴ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ በሰበር ችሎቱ የታየው ጉዳይ የውርስ ሃብት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ብ/ክ/መ/በቃፍታ ሑመራ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፤ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው አመልካች በተጠሪው ላይ ክስ የመሠረተው ከሟች እናቱ ወ/ሮ ዝማም አብርሃ በውርስ የተላለፈለት ንብረት (ቦታና ቤት) እንዲለቅለትና እንዲያስረክበው በመጠየቅ ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት የወረዳ ፍ/ቤትም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ አመልካች ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ ለሰጠው ውሣኔ ዋነኛ ምክንያት አድርጎ የጠቀሰው ከሣሽ (አመልካች) የሟች ልጅ ቢሆንም፤ ሟች በሕይወት እያሉ ባደረጉት ኑዛዜ ንብረቱ የእህታቸው ልጅ ለሆነው ተከሣሽ (ተጠሪ) ያወረሱ በመሆኑ ኑዛዜው የሚሻርበት ምክንያት የለም፡፡ የሚል እንደሆነም ከውሣኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤትም ተመሣሣይ ምክንያት በመስጠት ውሣኔውን ያፀና ሲሆን፣ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ደግሞ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል አከራካሪው ንብረት ለሁለቱም ይሁን በማለት ወስኖአል፡፡ አቤቱታው የቀረበውም በዚህ ላይ ነው፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 29-10-98

አቤቱታው በዚህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ጉዳይ ቀድሞ በመሃከላችን ተጀምሮ በነበረው ክርክር በሁለታችንም ስምምነት በእርቅ አልቆ የመጨረሻ እልባት አግኝቶአል:: እርቁ ለፍ/ቤት ቀርቦ ተመዝግቦአል በማለት አመልካች ክርክሩን በየደረጃው ላዩት ፍ/ቤቶች ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት ሳያገኝ የመቅረቱ አግባብነት መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው:: በዚህ መሠረትም ነጥቡን አቤቱታ ከቀረበባቸው ውሳኔዎች እና ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል::

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ማየት እንደቻልነው ቀደም ሲል በአመልካች እና በተጠሪው መካከል በተያዘው ጉዳይ ማለትም የውርሱን ሃብት በሚመለከት በፍ/ቤት መዝገብ ተከፍቶ ክርክር ተደርጎአል:: ክርክሩ የተካሄደው ለአሁኑ አቤቱታ መነሻ የሆነውን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ ባየው በቃፍታ ሑመራ ወረዳ ፍ/ቤት እንደሆነም ከመዝገቡ ተመልክተናል:: በሌላ በኩል ደግሞ ክርክሩ በፍ/ቤት ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት ተከራካሪ ወገኖቹ በ30/7/87 ዓ.ም በተደረገ የዕርቅ ስምምነት ለክርክራቸው እልባት መስጠታቸውና የእርቅ ስምምነቱም በመዝገብ ቁ. 60/87 በ6/8/87 ዓ.ም በፍ/ቤቱ ተቀባይነት አግኝቶ መመዝገቡን (መፅደቁን) አይተናል:: አመልካች ለስር ፍ/ቤቶች መቃወሚያውን ያቀረበው ይህን መሠረት በማድረግ ነው::

የእርቅንና የግልግልን ስምምነት ስለመመዝገብ በሚመለከት የተደነገገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 277 በንዑስ ቁጥር (1) እንዳመለከተው ክርክሩ በመሰማት ላይ ባለበት ጊዜ ተከራካሪዎቹ ወገኖች ነገሩን በእርቅ በመጨረስ የተስማሙ እንደሆነ ፍ/ቤቱ እርቁን ተቀብሎ በማፅደቅ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ያደርጋል:: የእርቅ ስምምነቱ ተጽፎና ተፈርሞ መቅረብ እንዳለበትና ፍ/ቤቱም እርቁን ተቀብሎ ከማፅደቁና ከመመዝገቡ በፊት ሕግንና ሞራልን የማይቃወም መሆኑን ሊረዳው እንደሚያስፈልግ ድንጋጌው ያመለክታል:: በመጨረሻም ፍ/ቤቱ እርቁን ከመዝገቡ ጋር ካያያዘው በኋላ በተከራካሪዎቹ ወገኖች አመልካችነት በእርቁ መሠረት እንዲፈፀም ትእዛዝ ወይም ፍርድ እንደሚሰጥ በንዑስ ቁ.(2) ተደንግጎአል:: እንግዲህ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ክርክሩ በተከራካሪ ወገኖች

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 29-10-98

ስምምነት በእርቅ ከተቋጨ እና ፍ/ቤቱም ተቀብሎ በማፅደቅ ከመዘገበው እንደማንኛውም የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ክርክር እንደሚቆጠር ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች እና ተጠሪ በመረጡአቸው ስድስት ሰዎች አስማሚነት (አስታራቂነት) ክርክራቸው በእርቅ የጨረሱ በመሆናቸው በዚህ ጉዳይ ሁለተኛ ክርክር ሊያካሂዱ አይችሉም፡፡ አመልካች ተጠሪን የከሰሰው ቀደም ሲል በተደረገው የእርቅ ስምምነት መሠረት ሊፈጽምለት ባለመቻሉ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ ከአፈፃፀም ክስ ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በእርቁ ስምምነት መሠረት የአመልካች ድርሻ የሆነውን ቤት ልቀቅ ሲባል የቀድሞውን (እኔም የኑዛዜ ወራሽ ነኝ) የሚለውን ክርክር ማንሣት አይችልም(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5(1))፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የተጠሪን ክርክር መቀበላቸው ትክክል አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበባቸው ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በወረዳ ፍ/ቤት፣ በከፍተኛ ፍ/ቤት፣ በጠ/ፍ/ቤት የተሰጡት እና በመጨረሻም በትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 10871 በጥቅምት 21 ቀን 98 ዓ.ም በተሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለባቸውም የተባሉት ውሣኔዎች በሙሉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ ውሣኔው ለሥር ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 29-10-98